‘ፍርደ ገምድል ዳኛ!’

**“የጌታንም ድምፅ። ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ። እኔም። እነሆኝ፥ እኔን ላከኝ አልሁ።” (ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 8**

እኔ እነቴን ተውኝ እንደ ተረ ተረት፤

ነገር ግን መልእክቴን እንደቀላል ነገር

በከንቱ አትጣሉት።

መንደሩ አገሩ በሆነበት አህጉር፤

እስኪ ልውሰዳችሁ

ወደ ኢትዮጵያ ምድር።

የተፈጥሮ እልቂት ሲመጣ አይቻለሁ

አንበጣ ሢወረን እንደ ዓውሎ ነፋስ

እህል ቀጠል ሳይለይ ፈጽሞ ሲጨርስ፤

በልቶ ሲያበቃ ግን በሞት ሲደመሰስ።

ጥፋቱ ቢበዛም ትንሽ ትልቅ ሣይል

እኔ አይቻለሁ ሕዝብ ተረባርቦ ወገኑን ሲመግብ፤

ነግ ለኔሳ ብሎ በፍጹም ሳያስብ።

የኔ መልእክት ይህ ነው

እንደዚያ ኢሳይያስ አምላክ ያስታወቀኝ

ፍርደ ገምድል ዳኛ

ኢትዮጵያን ሲያዛባት ቀኑ የሱ መስሎት፤

ይመከር ይገሰጽ

በቆፈረው ጉድጓድ እንዳይገባ ድንገት።

ወፏ ስትል ሰማሁ መንደሩ አገሩ በሆነበት አህጉር

ፍርደ ገምድል ዳኛ

እጅግ ይከበራል በአዲስ አበባ አገር።

ለምግብም ቢገዛ ፍርደ ገምድል ዳኛ፤

ወዮለት ታዛቤም ጸጥ ብሎ የሚተኛ።

እንደሻው አዳነ ደግሞ እንደመላኩ

ጎንደሬ ነኝ ብሎ ፈረደ በዓንዱአለም፤

ፈጣሪ አስታውቆኛል

እንደሻው አዳነ ፍርደ ገምድል ዳኛ

ይሁዳ ነው እንጅ ክርስቶስ አይደለም።

ፍርደ ገምድል ዳኛ

ኢትዮጵያን ሲያዛባት ቀኑ የሱ መስሎት፤

ይመከር ይገሰጽ

በቆፈረው ጉድጓድ እንዳይገባ ድንገት።

አገሪ ኢትዮጵያ ምን ግዛት አቋቋምሽ፤

መሪት ላራሽ ብለው

ለእልቂት ያጋለጡሽ?

ዓምላክን አይፈራ ወይ ባህል አይገታው

ወንድም ወገን ሳይለይ

በዱር በገደሉ ሲገል የለመደው፤

ከፈረንጅ በቀር ወገን እየጠላ ፍርሃትን ያዘለው

ከራባትን ሲለብስ ስልጣኔ መሰለው።

እንደሻው አዳነ ደግሞ እንደመላኩ

ጎንደሬ ነኝ ብሎ ፈረደ በዓንዱኣለም፤

ፈጣሪ ነግሮኛል

እንደሻው አዳነ ፍርደ ገምድል ዳኛ

ይሁዳ ነው እንጅ ክርስቶስ አይደለም።

ፍርደ ገምድል ዳኛ

ኢትዮጵያን ሲያዛባት ቀኑ የሱ መስሎት፤

ይመከር ይገሰጽ

በቆፈረው ጉድጓድ እንዳይገባ ድንገት።

**© ለምለም ጸጋው; July 3, 2012**

በኢትዮጵያ ምድር ያለአገባብ ተፈርዶባቸው በእስር ቤት ለሚማቅቁ

ሁሉ ለማስታወሻ የተጻፈ